ተገናኝተናል። ወንድሞቼ ሆላንድ እህተቼ ደንም ፈረንሳይ ስላሉ እንገናኛ ነበር።

ቁም ነገር፡- ጨተስ ልጅ ናቸው?

ፍቅም፡- በአጠቃላይ አስር ነን። አራት ሴቶች ስድስት ወንዶች። በአሁኑ ወቅት አራታችን እዚህ ስንሆን ስድስቱ በተለያየ አገር ናቸው።

ቁም ነገር፡- ወደአገር ቤት ከተመለስክ በኋላ እንዴት አዲስ ልበሳ የኒቨርሲቲ ገባህ?

ፍቅም፡- እንደመጣሁ ያን ጊዜ አድርገው የኔድኩትን ትምህርት መቀጠል አለብኝ የሚል ሀሳብ ነው የነበረኝ። ጣሊያን ትምህርቱን ስማሪውም እንዲያ የመጨረሻ ሁለት ኮርሶች ባለመውሰዴ ሳቢያ መመረቅ አልቻልኩም። የወሰድኳቸው ኮርሶችና ውጤቴ ግን ጥሩ ስለነበሩ ያንን አያጋር ትምህርቱን ለመቀጠል እንድችል ሚመልከታ አስገባሁ። ማመልከቻውን ላስገባ ስል የሚያውቁኝ አንዳንድ ሰዎች «እንዴት ከልጆችህ ጋር ለመማር ትጠይቃለህ?» ያሉኝ ነበሩ። እኔ ግን ጓጊ ጎሪሪዱን ማግኘት ስለነበረብኝ ምንም ቅሬታ ሳያሰማኝ ጠየቅሁ። የአካዳሚክ ኮሚሽኑ ጥያቄዬ ግራ ሳይጋባቸው አልቀረም። ውጤቴን ሲመለከቱት ጥሩ ነው። ግን ትምህርቱን ከቋረጥኩ ከ20 ዓመታት በኋላ ስለመጣ ከመጨረሻ «ወደጣ ሊያን ስትሄድ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ስለነበርክ በዚያ ነው መቀጠል የምትችለው» አሉኝ። ደስ እያለኝ ትምህርቱን ጀመርኩ።

ቁም ነገር፡- ቀን ነው ማታ?

ፍቅም፡- ምን ነህ? ቀን ነው እንጂ። ዶርም ሁሉ ወስጄ ምግብ አብሬያቸው እኖባለሁ ከ19 እና ከ20 ዓመት ልጆች ጋር እኩል ቁጭ ብዬ ተምሬ በ1989 ዓ.ም ጣሊያንን አገኘሁ። የሚገርምህ ያን ጊዜ ከእኔ ጋር ተማሪ የነበሩ ልጆች ከ20 ዓመት በኋላ ስመጣ እዚያው አስተማሪዎች ሆነው ተገናኝተናል።

ቁም ነገር፡- ትምህርት እስከትጨርስ ኑሮና ከሬማት ብቻ ታደርገ ስለነበር እንደልጅ ተማሪ ነበር የምትታየው ደግሳለህ?

ፍቅም፡- በትክክል! አንድም ቀን ሁለን ከነከሪባቱ ሳላወልቅ ነው የተማርኩት። ድሮ ጀምሮ ኩት ማድረግ ደስ ይለኛል። በዕድሜም ከልጆቹ ከፍ ስለምልና ከመምህራን ጋር ስለነበር ወዲያ ወዲህ የምለው ብዙ ስምች አስተማሪ ወይም የአስተዳደር ሠራተኛ ነበር የሚያደርጉኝ። ከፍል ውስጥ ራሱ አንዳንድ አስተማሪዎች «አስኪ አንዳንድ ቀን እንኳን ተማሪ ምሰልና ጫኬት አድርገሽ ይሉኝ ነበር። እኔ ግን ከነኮትና ከነከራሜ ተምሬ ተመረቅሁ።

ቁም ነገር፡- ጣሊያን የነበርክ ጊዜ ስታዲየም ትገባ ነበር?

ፍቅም፡- እም እገባለሁ። ኳስ በጣም ነው የምወደው።

ቁም ነገር፡- የማን ደጋፊ ነህ?

ፍቅም፡- እሁን ድሬስ የኢንተር ሚላን ደጋፊ ነኝ።

ቁም ነገር፡- ጨትየጅያ ትልቁን የእንግሊዝና ጣሊያ ማነበብ እንዴት ጀመርክ?

ፍቅም፡- ትምህርት ሳልጨርስ ነው ኢ.ትዮጵያ ቴሌቪዥን የጨና አንባቢነት የጀመርኩት።

ቁም ነገር፡- እንዴት?

ፍቅም፡- ማስታወቂያ ወጥቶ ስለነበር በንደኛዬ ገፋፊነት ሂጂ የተመዘገብኩት የመጨረሻ ቀን ነው። የመጀመሪያ ፈተና ሰለት 40 ሰዎች ነበርን ኢንተርቪው ከተደረገልን በኋላ ድምፅ ተፈተንን። በሌላ ቀን ደግሞ የስክሪን ፈተና ወስደን የተመረጣችሁ ትን እንደውልላችኋለን አሉ። ማስታወቂያ ከወጣ ከረጅም ጊዜ በኋላ ስለነበር ስፈተና የጠሩን በቶሎ ውጤቱን ጨርሰው ይደውሉሉ የሚል እምነት አልነበረኝም። ከዚያ እኔና ገሊላ የምትባል ልጅ አልፈን ገባን።

ቁም ነገር፡- ስንት ዓመት ዜና ስነበብክ?

ፍቅም፡- ስድስት ዓመት ያህል አንብቤአለሁ።

ቁም ነገር፡- ለምን የወጣህ?

ፍቅም፡- የእንግሊዝኛ ዜና እንደሌላው ዜና አይደለም። ዜናውን በአብዛኛው የምታቀርበው ሰውጪው ኮሚውኒቲ ነው። በአርገጥ የአገር ውስጥ ሰዎችም ይከታተሉናል። ስዓቱን ያዛበው እንደሆነ ከምሽቱ 4:30 ነው የሚቀርበው። ቀን የተለያየ ሥራ ስትሰራ ቶይተህ እንደማንኛውም ሰው ለመኝታ በመሄዳህ ስዓት አንተ ስንባብ ስቁዲዮ ነህ። የዜና ሰዓቱ ከ20 እስከ 25 ደቂቃ የሚቆይ ቢሆንም ከምሽቱ ሁለት ስዓት እስከ አምስት ስዓት ተጩል ድረስ ቢትህ አትንገም። ለዚያውም ዜና አንባቢ ምሽት 12 ስዓት የሚያነበውና በጊዜ ወደቤቱ የሚሄደውም ማታ የሚያመሽውም እኩል ነው የሚከፈለው።

ቁም ነገር፡- ምን ያህል?

ፍቅም፡- በፊት ለአንድ ጊዜ ንባብ 40 ብር ነበር። ትንሽ ቆይቶ 80 ብር ሆነ። ያም ቢሆንም በሌላ አገር ለዜና አንባቢ ኮሚሽፈለው ከፍያ ጋር አይደራረስም። ዜና ማለት የጣቢያው ትልቅ ፕሮግራም ነው። ሌላው ነገር ደግሞ አንድ ሰው ሰብቡ ጊዜ ዜና አንባቢ ሆኖ ሲቆይ ህዝብም

ወደገጽ 38 ዞሯል

ሮኬት የልብስ ንፅህና መስጫ
Rocket Laundry
አንኳን ሰፋሲካ በዓል አደረሳችሁ!
☞የሱፍ ልብስ ☞ የሀገር ባህል ልብስ
☞ የሙሽራ ልብስ ☞ብርድ ልብስ ☞ መጋረጃ ☞የመኪና ወንበር ልብስ
☞ የመሬት ምንጣፍ እናጥባለን
☞ የቆዳ ልብሶችን እናቀልማለን
☞ልብስዎ በአስቸኳይ እንዲደርስልዎት ከፈለጉ ፈጣን አገልግሎት በመስጠት የታወቅን ነን
አገልግሎታችን ፈጣን ጥጋችን ተመጣጣኝ!
አድራሻ፡- ቁጥር 1 ታይሉ ገ/ስላሴ ጉዳና አክሱም ሆቴል አካባቢ ☎ 181507
ቁጥር 2 አዋሬ ታክሲ ማዞሪያ አካባቢ
☎ 225592 ፖ.ሣ.ቁ. 170050 አ.አ